# <u>ያስውጪ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገቡ እቃዎች የወጣውን ደንብ ለማስፈፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 66/2004</u>

ያስውጪ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገቡ እቃዎች ተሻሽሎ የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 88/1995 ለማስፈፀም የወጣውን መመሪያ አሁን ካለው የቴክኖሎጂ ሽግግር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የእቃዎች ዋጋ መናር ጋር ተያይዞ አፈፃፀሙን ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የደንቡን ዓላማ የሚፃረሩ አድራጐቶች በማስወገድ ያልተፈቀዱ የንግድ እቃዎች እንዳይገቡ በመቆጣጠርና በደንቡ የተፈቀዱትንም እቃዎች አግባብ ባለው መልኩ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት በማስፈለጉ፤

ያስውጪ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገቡ እቃዎች ተሻሽሎ በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 88/1995 አንቀፅ 3/1/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "ያስ ውጪ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገቡ እቃዎች የወጣውን ደንብ ለማስፈፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 66/2004 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፡-

1) **"የግል መገልገያ"** ማለት ከአንድ ግለሰብ አገልግሎት ጥቅምና ይዞታ ጋር የተቆራኘ በሕይወት ባለ ጊዜ ለአጭር ወይም ለረዥም ጊዜያት የሚጠቀምበት ተንቀሳቃሽ፣ ለንግድ የማይውል እቃ ሲሆን የቤት ውስጥ መገልገያን ይጨምራል።

2) **"የቤት ውስጥ መገልገያ"** ማለት በአንድ ጣሪያ ስር ከሚኖር ቤተሰብ ጥቅም፣ አገልግሎት ይዞታ እና ፍጆታ ጋር የተቆራኙ ልብሶች፣ ጫማዎች፣ የግል ንፅህና መጠበቂያዎች፣ የመዋቢያ፣ የመመገቢያ፣ የቤትና የማዕድ ቤት እቃዎችን እና እነዚህኑ የመሳሰሉ እቃዎች ናቸው፡፡

3) **"የንግድ መጠንና ባህሪ ያለው እቃ"** ማለት ከግል ወይም ከቤተሰብ ፍጆታ በላይ የሆኑና በሽያጭ ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ ጥቅም ላይ በማዋል ትርፍ ሊያስገኝ የሚችል መጠን ያለው እቃ ነው።

4) “**የመንገደኞች የግል መገልገያ**“ ማለት ከአንድ ተጓዥ ግለሰብ አገልግሎት ይዞታ ጋር የተቆራኙ በጉዞ ላይ እና በሚያደርጋቸው የጉዞው ቆይታዎች የሚጠቀምባቸው ተንቀሳቃሽ ያገለገሉ ወይም አዳዲስ በጊዜያዊነት ወይም ለዘለቄታው የሚጠቀምባቸው አላቂ ወይም ቋሚ እቃዎች ናቸው።

5) “**የስጦታ እቃ**” ማለት ማንኛውም በውጪ ሀገር ያለ ሰው ወይም ድርጅት ኢትዮጵያ ውስጥ ላለ፣

   a. ለቤተሰብ፣ ዘመድ ወይም ጓደኛ የሚላኩና የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን፣
   b. ለመንግስታዊ ባለበጀት መ/ቤት እና ሲቪል ማህበራት፣ የሚላክ እና ከተቋሞቹ ሥራ ጋር የተያያዙ ለተግባራቸው አጋዥ የሆኑ ዕቃዎች፣
   c. ለኃይማኖት፣ ለትምህርት፣ ለህክምና ተቋማት ፣ ሲቪል ማህበራት አገልግሎት እንዲውሉ የሚላኩ እና ለተቋሞቹ ወይም ለድርጅቶቹ ተግባራት ብቻ የታቀዱ እቃዎች ነው።

6) “**መንግስታዊ ባለበጀት መ/ቤት**” ማለት በበጀት የሚተዳደር የፌደራል ወይም የክልል መንግስታዊ መ/ቤት ነው፡፡

7) “**የናሙና እቃ**” ማለት የንግድ ድርጅት በተሰጠው አገልግሎት የሚሸፍኑ ወይም በማምረቻ ፈቃዱ ለሚያመርተው ምርት ግብዐት እና ለሙከራ የሚውል ዕቃ ነው፡፡

8) “**የንግድ ማስተዋወቂያ ዕቃ**” ማለት የአንድ ሰው ወይም ድርጅት ወይም ተቋም ምርት አርማ፣ መልክ፣ ስም ወይም መለያ ያለበትና ለተጠቃሚዎች በማስተዋወቂያነት በነፃ የሚታደል ወይም በተፈቀደ የንግድ ትርዒት ለኤግዚቢሽን በጊዜያዊነት ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ የሚወጣ ለንግድ የማይውል እቃ ነው።

9) “**በጊዜያዊነት ወደ አገር የሚገባ ዕቃ**” ማለት ከቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ከቱሪዝም፣ ከባህል ልውውጥ፣ ከግንባታ ሥራና ከምክር አገልግሎት ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚጠበቅ ኃላፊነት ጋር በተያያዘ ለሰላም ማስከበር ወይም ሌላ ተልዕኮ የሚውል፣ ለዓለም አቀፍ ስብሰባ፣ ኮንፍረንስ፣ ሲምፖዚየም፣ ወርክሾፕ አገልግሎት ጋር የተያያዘ የመጣበትን ምክንያት ካጠናቀቀ በኋላ በህግ መሠረት ለሌላ ሲተላለፍ የሚችል የሚዘዋወር ወይም በመጣበት አኳኋን ወደ ውጪ አገር የሚመለስ ዕቃ ነው፡፡

10) “**ዓለም አቀፍ ድርጅቶች**” ማለት ሁለት እና ከሁለት በላይ በሆኑ ሀገሮች የተቋቋሙና ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ድርጅቶች ማለት ነው።

11)“ደንብ” ማለት ያለውጪ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገቡ እቃዎች ተሻሽሎ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 88/1995 ነው።

12) “ባለስልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ነው።

## 13) ዓላማ

ይህ መመሪያ በመደበኛው የንግድ ስርዓት ላይ ተፅዕኖ የማያደርጉ በአብዛኛው የገንዘብ ምንጫቸው ከኢትዮጵያ ውጪ የሆኑ እቃዎችን ካለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር እንዲገቡና ስተፈቀደላቸው ተግባር እንዲውሉ ለማስቻል ነው።

## 4. የአፈፃፀም ወሰን

ይህ መመሪያ በደንቡ አንቀፅ 2 በተዘረዘሩትና የባለስልጣኑ መ/ቤት እንደ አስፈላጊነቱ በደንቡ አንቀፅ 3/2/ በተሰጠው ስልጣን መሠረት እንዲገቡ በሚፈቅዳቸው እቃዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## 5. ያለውጪ ምንዛሪ ክፍያ የሚገቡ እቃዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ ባለው ሠንጠረዥ ላይ በተገለፀው ሁኔታ፣ ዓይነትና መጠን እቃዎች ያለውጪ ምንዛሪ ክፍያ ይገባሉ።

## 6. ፈቃድና ማስረጃ አስፈላጊ ስለመሆኑ

1) እንደ እቃው ባህሪ አይነት አግባብ ባለው ተቆጣጣሪ መ/ቤት የሚሰጠው ማስረጃ መቅረቡ እንደተጠበቀ ሆኖ ካለውጪ ምንዛሪ ክፍያ እንዲገባ የሚጠየቀው እቃ ወደ አገር ከመግባቱ አስቀድሞ ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ ላይ በተመለከተው መሠረት አስቀድሞ ስለመፈቀዱ ህጋዊ ማስረጃ ለባለስልጣኑ መቅረብ አለበት።
2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ አንድ የተገለፀው ቢኖርም በአገሪቷ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት የመግቢያ ወደብ ወደ አገር የመጡ ወይም በቀጥታ በአገሪቱ የተቋቋሙ ደረቅ ወደቦች የተከማቹ ዕቃዎች በወደቡ መጋዘን እያሉ ለዕቃዎቹ የሚያስፈልጉ ማስረጃዎች ተሟልተው ሲቀርቡ ይችላል፡፡

## 7. ስለቀረጥ ታክስ እና ዋስትና

በሕግ ወይም በዓለም አቀፍ ስምምነት መሠረት በሙሉ ወይም በከፊል ከቀረጥና ታክስ ነፃ ልዩ መብት ከተሰጠው ሰው ወይም ድርጅት በስተቀር ካለውጭ ምንዛሪ ክፍያ የሚገባ እቃ በሙሉ ፀንቶ በሚገኘው ታሪፍና ደንብ መሠረት ቀረጥና ታክስ ይከፈልበታል ወይም እንደአግባብነቱ ለቀረጥና ታክሱ ዋስትና ይያዝበታል።

## 8. በልዩ ሁኔታ ያለውጭ ምንዛሬ ክፍያ ዕቃ እንዲገባ ስለመፍቀድ፣

1) የዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ ከሚገኘው ሠንጠረዥ ውጪ የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ስራ አስኪያጅ በደንቡ አንቀፅ 3/2/ መሠረት ያለውጭ ምንዛሬ ክፍያ ዕቃ እንዲገባ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
2) በማኒፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት የተሰማሩ የውጭ ኢንቨሰተሮች ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ ኢንቨስተሮች ለተሰማሩበት የሥራ መስክ አጋዥ የሆኑ የካፒታል ዕቃ ያልሆኑ ሌሎች ዕቃዎች ወይም በቀረጥ ማበረታቻ ሳስገባቸው ማሽኖች ለመለዋወጫነት የሚውሉ ዕቃዎችና ሌሎች አክሰሰሪዎች በአገር ውስጥ ሲመረቱ ወይም ሲገኙ የማይችሉ መሆኑ ከተረጋገጠ የገንዘብ ገደብ ሳይደረግባቸው በፍራንኮ ቫሉታ ማስገባት እንዲችሉ ይፈቀዳል፡፡
3) የባለሥልጣኑ የቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ማስተባበሪያና ድጋፍ ዘርፍ ም/ዋ/ዳይሬክተር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ አንድ እና ሁለት ላይ ከተገለፀው ውጪ በልዩ ሁኔታ ያለውጭ ምንዛሬ ክፍያ ዕቃ እንዲገባ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## 9. ክልከላ

1) በመመሪያው አንቀፅ 8 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የንግድ መጠንና ባህሪ ያለው ዕቃ ወይም ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ላይ ከተመለከተው ውጪ ካለውጭ ምንዛሪ ክፍያ እቃዎችን ወደ ኢትዮጵያ ማስገባት ክልክል ነው።
2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ቢኖርም በሰንጠረዡ ተራ ቁጥር 13 ላይ የተመለከቱት ሰዎች ያመጡት ዕቃ በዝርዝሩ ያልተመለከተ ቢሆንም እንኳ የግል መገልገያ ዕቃ ከሆነና በቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ከተወሰነ ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ መግባት ይችላል፡፡

## 10. ሕጋዊ እርምጃ

1. በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 9 ሳይ የተመለከተውን ክልከሳ የተሳለፈ ሰው ከተፈቀደው በሳይ በትርፍነት ወይም ከተፈቀደው ውጪ ለመጣው እቃ እንደማጭበርበር ተቆጥሮ የጉምሩክ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሣኔ እልባት ለመስጠት በወጣው የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መመሪያ መሠረት ይወሰናል።
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ አንድ በተመለከተው መሠረት ያልተስተናገደ ወይም የማይስተናገድ እቃ በሙሉ ደንቡን በመተሳለፍ ምርመራው ተጣርቶ ለሕግ ይሳካል።

## 11. የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጐች

1. ያለውጪ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገቡ እቃዎች ተሻሽሎ የወጣውን ደንብ ለማስፈፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 9/1996 እና መመሪያ ቁጥር 27/1998 በዚህ መመሪያ ተሽሯል።
2. በዚህ መመሪያ በሚታዩ ጉዳዮች ሳይ አስቀድመው የነበሩ አሠራሮችና ልማዶች ይህን መመሪያ የሚቃረኑ ከሆኑ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

## 12. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመፅናቱ በፊት ተጀምረው እልባት ወይም ውሣኔ ያሳገኙ በመመሪያው ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሠረት ውሣኔ ሊያገኙ ይችሳሉ።

## 13. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ------------ ቀን 2003 ዓም

መሳኩ ፈንታ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ዋና ዳይሬክተር

# ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር የሚገቡ እቃዎች የአገባብ ሁኔታዎች

| ተቁ | ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ የሚገቡ የእቃዎች ዓይነት | ያለውጪ ምንዛሪ ክፍያ እንዲገባ የተፈቀደው የእቃ መጠን እና FOB ዋጋ በአሜሪካን ዶላር | ያለውጪ ምንዛሪ እቃዎችን ለማስገባት የሚቀርብ ማስረጃ |
|---|---|---|---|
| 1 | የዲፕሎማቲክና የቆንስላ ሚሲዮኖች ለታወቁ አገልግሎቶች የሚያስገቧቸው እቃዎች | ለዲፕሎማቲክ ወይም ቆንስላ ሚሲዮኖች አገልግሎት የሚውሉ እቃዎች በሙሉ | በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጦ የሚቀርብ የኤምባሲው ማስረጃ |
| 2 | የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ለታወቁ አገልግሎታቸው የሚያስገቧቸው እቃዎች | ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች አገልግሎት የሚውሉ እቃዎች በሙሉ | በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጦ በዓለም አቀፍ ድርጅቱ የሚቀርብ ማስረጃ |
| 3 | የእርዳታ ድርጅት ለሚሰጠው አገልግሎት የሚጠቀምባቸው እቃዎች | ለእርዳታ ድርጅቱ አገልግሎት የሚውሉ እቃዎች በሙሉ | በግብርና ሚኒስቴር ወይም በሚመለከተው የመንግስት መ/ቤት ተረጋግጦ የሚቀርብ ማስረጃ |
| 4 | የዲፕሎማቲክና የቆንስላ ሚሲዮኖች፣ ሹማምንቶች እና ሠራተኞች የሚያስገቧቸው የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች | ለሹማምንቱና ለሠራተኞች አገልግሎት የሚውሉ የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች በሙሉ | በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የኤምባሲ ማስረጃ |
| 5 | የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሹማምንቶችና ሠራተኞች የሚያስገቧቸው የቤት ውስጥና የግል መገልገያ እቃዎች | ለሹማምንቶችና ለሠራተኞች አገልግሎት የሚውሉ የግልና የቤት ውስጥ መገልገያዎች በሙሉ | በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የዓለም አቀፍ ድርጅት ማስረጃ |
| 6 | የዓለም አቀፍ እርዳታ ድርጅቶች ሹማምንቶች እና ሠራተኞች የሚያስገቧቸው የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች | ለሹማምንቶችና ለሠራተኞች አገልግሎት የሚውሉ የግልና የቤት ውስጥ መገልገያዎች በሙሉ | በግብርና ሚኒስቴር ወይም በሚመለከተው የመንግስት መ/ቤት ተረጋግጦ የሚቀርብ ማስረጃ |
| 7 | የኢትዮጵያ መንግስታዊ ባለበጀት መስሪያ ቤት በስጦታ፣ በእርዳታ ወይም በልገሣ የሚያስገቧቸው ከሥራቸው ጋር የተያያዘ ለተግባራቸው አጋዥ እቃዎች | መ/ቤቶቹ ለተግባራቸው አጋዥ የሆኑትና ለስራዎቻቸው የሚያስፈልጉዋቸው እቃዎች ብቻ | የባለበጀት መ/ቤቱ ማረጋገጫ ማስረጃ |
| 8 | የሲቪል ማህበራት በስጦታ፣ በእርዳታ ወይም በልገሳ የሚያስገቧቸው ከሥራው ጋር የተያያዘ ለተግባራቸው አጋዥ የሆኑ እቃዎች | ለተግባራቸው አጋዥ የሆኑትና ለስራዎቻቸው የሚያስፈልጋቸው ዕቃዎች ብቻ | ስጦታ፣ እርዳታ፣ ወይም ልገሣ የተደረገበት የተረጋገጠ የምስክር ወረቀት እና ማህበሩ የተቋቋሙበትን ሠነድ |

| ተቁ | ያስውጭ ምንዛሬ ክፍያ የሚገቡ የእቃዎች ዓይነት | ያስውጪ ምንዛሬ ክፍያ እንዲገባ የተፈቀደው የእቃ መጠን እና FOB ዋጋ በአሜሪካን ዶላር | ያስውጪ ምንዛሬ እቃዎችን ለማስገባት የሚቀርብ ማስረጃ |
|---|---|---|---|
| 9 | የኃይማኖት፣ የትምህርት፣ የህክምና ወይም የሞያ ተቋማት ወይም ድርጅቶች ለተቋሞቹ ወይም ለድርጅቶቹ ተግባራት ብቻ የታቀዱ በስጦታ ወይም በእርዳታ ከውጪ ሀገር የሚያስገቧቸው ለንግድ የማይውሉ እቃዎች | ከተቋሞቹ ወይም ከድርጅቶቹ ተግባራት ጋር በታቀደው መጠን ሆኖ ለንግድ የማይውሉ | ስጦታ፣ እርዳታ፣ የተደረገበት የተረጋገጠ የምስክር ወረቀት እና ማህበሩ የተቋቋመበት ሰነድ |
| 10 | ለቤተሰብ፣ ለዘመድና ለጓደኛ ከውጪ ሀገር በስጦታና በልገሣ የሚገቡ ለንግድ የማይውሉ ተሽከርካሪን የማይጨምር የግልና የቤት ውስጥ መገልገያዎች | ባለሥልጣኑ በሚያወጣው የግል መገልገያ ዕቃዎች ዝርዝር መሠረት | |
| 11 | በማንኛውም መስክ ላስ ተመራማሪ ፣ከምርምር ስራው ጋር የተያያዘ በስጦታና በልገሣ የሚገቡ እቃዎች | ከምርምር ስራው ጋር የተያያዘ እና የተዛመደ | ከምርምር ተቋሙ የሚገባው እቃ ለምርምር ስራው መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ |
| 12 | በኢትዮጵያ ውሰጥ ለመኖር ለመጀመሪያ ጊዜ የሚመጡ ግለሰቦች የሚያስገቧቸው ተሽከርካሪን የማይጨምር የግልና የቤት ውስጥ መገልገያዎች | - የንግድ ባህሪና መጠን የሌላቸው<br>- የግል መገልገያ ዕቃዎቹ ከ5,000 ካልበለጠ ከቀረጥ ነፃ ይገባሉ፣ | - በኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር የተሰጣቸው የመኖሪያ ፈቃድ<br>- ከውጭ ጉዳይ ሚ/ር ወይም አግባብ ካለው መ/ቤት የተሰጠ ማረጋገጫ |
| 13 | በልዩ ልዩ ምክንያት ውጪ ሀገር ቆይተው ጠቅልለው የሚመለሱ ኢትዮጵያን እና የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጪ ዜጐች ለግል ስራቸው የሚያስገቧቸው እና የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች እና የግልና የቤት ውስጥ መገልገያዎች | የንግድ ባህሪና መጠን የሌላቸው አይነታቸው በሰንጠረዥ 2 የተዘረዘሩት | -ከነበሩበት ሀገር ያለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጠቅልለው ስለመግባታቸው የሚገልፅ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ማስረጃ<br>-አስመጪው በነበረበት ሀገር በሞያው ወይም በግል መሣሪያው ሲሰራበት የነበረ መሆኑን የሚያረጋግጥ የቅጥር ወይም የንግድ ስራ ማስረጃ እና ይህንኑ የሚገልፅ ውጪ ሀገር በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ /ቆንስላ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ማስረጃ |

| ተቁ | ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ የሚገቡ የእቃዎች ዓይነት | ያለውጪ ምንዛሪ ክፍያ እንዲገባ የተፈቀደው የእቃ መጠን እና FOB ዋጋ በአሜሪካን ዶላር | ያለውጪ ምንዛሪ እቃዎችን ለማስገባት የሚቀርብ ማስረጃ |
|---|---|---|---|
| 14 | አግባብ ባለው የመንግስት መስሪያ ቤት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያገኙ በውጭ ሀገር በዘላቂነት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና የውጪ ዜግነት ያላቸው የኢትዮጵያ ተወላጅ ባለሀብቶች ለኢንቨስትመንት ሥራቸው የሚሆን የካፒታል እቃ ጥሬ እቃ፣ እስከ ኮሚሽኒንግ ደረጃ የሚበቃ እና ለግል መገልገያ የሚያስገባቸው መሣሪያዎች | - ከኢንቨስትመንት ጋር ብቻ የተያያዘ የካፒታል እቃ፣ ከኢንቨስትመንቱ ሥራ ጋር የተያያዘ እና የተዛመደ ለሙከራ ምርት የሚበቃ ጥሬ እቃ በተፈቀደው መጠን፣<br>- ለግል መገልገያ የሚያስገባቸው መሳሪያዎች ከ10,000 FOB ዋጋ ያልበለጠ | ዕቃዎቹ ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ ከሆነ ከወጪ እና ሌሎች እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ፅ/ቤት የሚሰጥ ማስረጃ |
| 15 | በስፖርት፣ በኪነትና በመሳሰሉት ለግለሰቦችና ድርጅቶች የሚላኩ ሽልማቶች፣ ለሽያጭ ያልመጡ ለስጦታ ብቻ የሚውሉ ዋንጫዎች ሜዳሊያዎች እና ሌሎች ሽልማቶች | የንግድ ባህሪ እና መጠን የሌላቸው ወይም ለሽያጭ ያልመጡ ለአሸናፊው በሽልማት የተሰጡ ዋንጫዎችና ሜዳሊያዎች ሌሎች ሽልማቶች | ከሸላሚው የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካለው የመንግስት መ/ቤት የተረጋገጠ ማስረጃ |
| 16 | ወደ ውጪ ሀገር ለሚላኩ እቃዎች በግብዐትነት የሚያገለግሉ እቃዎች እንደ መለያ ዘሮች እንዲሁም መጠቅለያዎችና መያዣዎች የመሳሰሉት | ወደ ውጪ ለሚላከው እቃ አገልግሎት ብቻ የሚውል መለያ ዘሮች መጠቅለያዎችና መያዣዎች እና የመሳሰሉት፣ | በወጪ ንግድ ማበረታቻ ሥርዓት የታቀፈ ለመሆኑ ከንግድ ሚኒስቴር የተሰጠ ማረጋገጫ |
| 17 | ለሽያጭ ያልመጡ ስጦታዎች፣የንግድ ናሙናዎች እና የማስታወቂያ እቃዎች | - የማስታወቂያ እቃዎች ከሆኑ የምርቱን ዓርማ፣ የድርጅቱን ስም፣ ልዩ መለያ ወይም ምልክት ያላባቸው ለንግድ የማይውሉ ሆነው የFOB ዋጋቸው ከ5,000.00 ያልበለጡ፣<br>- ስጦታዎች ወይም የንግድ ናሙናዎች የንግድ መጠን የሌላቸው ሆነው የFOB ዋጋቸው ከ4000.00 የማይበልጡ | የመጡት እቃዎች በንግድ ፈቃድ ለሚያካሂደው ንግድ ወይም አገልግሎት መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ |
| 18 | አገር ውስጥ ገብተው የማይቆዩ በተደጋጋሚ እቃ የሚመጣባቸው ኮንቴነሮች፣ ሣጥኖች፣ ጣሣዎች፣ ጠርሙሶች ማድጋዎችና ሌሎች መያዣዎች | ይዘዋቸው በሚመጡት ገቢ እቃዎች መጠን | ለገቢ እቃዎች የሚቀርቡ ሠነዶች |

| ተቁ | ያስውጭ ምንዛሪ ክፍያ የሚገቡ የእቃዎች ዓይነት | ያስውጪ ምንዛሪ ክፍያ እንዲገባ የተፈቀደው የእቃ መጠን እና FOB ዋጋ በአሜሪካን ዶላር | ያስውጪ ምንዛሪ እቃዎችን ለማስገባት የሚቀርብ ማስረጃ |
|---|---|---|---|
| 19 | ለአካል ጉዳተኞች የሚመጡ ወይም የሚላኩ ለንግድ የማይውሉ እቃዎችና መሣሪያዎች | ለአካል ጉዳተኞች ብቻ የሚመጡ እቃዎችና መሣሪዎች በሙሉ | ከሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚቀርብ ማረጋገጫ |
| 20 | የጉደሉ ወይም ብልሽት ያለባቸውን እቃዎች ለመተካት አቅራቢው ከአስመጪው ጋር ባለው የዋስትና ስምምነት መሠረት የሚገቡ እቃዎች | በጉደሉ ወይም በብልሽት የመጡትን እቃዎች የሚተኩ መጠን ያላቸው | ለመጉደሉ ወይም ብልሽት ለለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ እና ላኪው ለአስመጪው የሰጠው ዋስትና /ዋራንቲ/ የሚገልፅ ማስረጃ |
| 21 | ለአንድ ተቋም መደበኛ ስራ እና ለግለሰብ ጤና እጅግ አስፈላጊ የሆኑ በአፋጣኝ ሲገቡ ካልቻሉ ስራው ላይ እንቅፋት የሚፈጥሩ ወይም ህይወትን አደጋ ላይ ሲጥሉ የሚችሉ እቃዎች | እንደ አስፈላጊው እቃ፣ ወይም መለዋወጫው ዓይነትና መጠን፣ ወደ ሀገር የሚገባው መድሃኒት ከሆነ የFOB ዋጋው ሳይወሰን በሚያስፈልገው መጠን፣ የመኪና መለዋወጫ ከሆነ ሞተር ካምቢዮ፣ ዲፈረንሻልን ሳይጨምር ብልሽት በገጠመው ልክ መጠን | ከድርጅቱ ወይም ከሐኪም /ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር/የሚቀርብ ማስረጃ የመኪና መለዋወጫ ከሆነ ሊብሬ መቅረብ አለበት |
| 22 | መንገደኞች ይዘዋቸው የሚመጡት እቃዎች | በባለሥልጣኑ በሚያወጣው የግል መገልገያ ዕቃዎች ዝርዝር መሠረት | |
| 23 | በጊዜዊነት ወደ ሀገር ገብተው ተመልሰው የሚወጡ እቃዎች | በተፈቀደው መጠንና ዓይነት | ከሚመለከተው መንግስታዊ መ/ቤት ጋር የተደረገው ስምምነት ማስረጃ ወይም አግባብነት ያለው ማስረጃ |